በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት በግዥና ንብረት አስተዳደር ላይ የተከናወነ የክትትል ኦዲት ሪፖርት

ጥር 2008 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ክፍል አንድ 3
መግቢያ 3
የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ሥልጣንና ተግባር 3
የክትትል ኦዲቱ ዓላማ 4
የክትትል ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ 4
የክትትል ኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች (Standards of follow up Audit) 5
ክፍል ሁለት 6
በኦዲት ክትትል የተገኙ ግኝቶች 6
የኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የግዥ ሂደትን በተመለከተ 6
የቼክ ክፍያ አፈፃፀምን በተመለከተ 8
የማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች በኪራይ በተመለከተ 9
በግዥ፣ በእርዳታ እና በስጦታ የሚያገኛቸው ንብረቶችን አመዘጋገብ በተመለከተ 11
ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠን /Minimum& Maximum Stock Level/ መቀመጡን በተመለከተ 13
ንብረቶች ገቢና ወጪ ሥርዓትን በተመለከተ 15
የነዳጅ ታንከሮች ካሊብሬት መደረጋቸውን በተመለከተ 18
የግንባታ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች የመለዋወጫ አቅርቦት በተመለከተ 19
የተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች ጥገና ሥርዓትን በተመለከተ 21
አገልግሎት የማይሰጡ መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎችና መለዋወጫዎችን በተመለከተ 23
የነዳጅ አጠቃቀምና የስምሪት መመሪያ በተመለከተ 24
ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ/Inventory/ በተመለከተ 25
የመረጃዎች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መያዛቸውን በተመለከተ 26
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በክዋኔ ኦዲቱ ያስገኘው ጥቅም በተመለከተ 26
ክፍል ሶስት 28
መደምደሚያ 28
ክፍል አራት 30
በክትትል ኦዲቱ (Follow up Audit) የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች 30
አባሪ 1 32

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. በ1940ዎቹ መጀመሪያ የህዝብ ስራዎች ሚኒስቴር ሥር የውሃ ልማት ኤጀንሲ የሚባል ተቋም የተቋቋመ ሲሆን በአሜሪካ መንግስት እርዳታ "point four" በመባል ከተመሰረተው ተቋም ጋር በቅርበት ይሰራ ነበር::
2. ግብጽ እና ሱዳን በየሀገሮቻቸው የአባይ ሸለቆ ጥናት በመጀመራቸው ኢትዮጵያም የአባይንና የሌሎች ወንዞች ተፋሰሶችን ለማጥናት ተጠሪነቱ ለህዝብ ሥራዎች ሚኒስቴር የሆነ የአባይ ተፋሰስ ጥናት የሚያካሂድ ክፍል ተቋቋመ፡፡ የውሃ ልማት ኤጀንሲ እና የአባይ ተፋሰስ ጥናት ተጠሪነታቸው ለህዝብ ሥራዎች ሚኒስቴር ሆኖ እስከ 1975 ዓ.ም ከቀጠሉ በኋላ በአንድነት የኢትዮጵያ ውሃ ልማት ባለስልጣን ተብለው ተጣመሩ፡፡ በመላ ሀገሪቱም ስምንት የውሃ ልማት ቀጠናዎች ተዋቀሩ፡፡ ይህ አደረጃጀት ለአራት አመታት ያህል ከቀጠለ በኋላ በ1979 ዓ.ም ብሄራዊ የውሃ ልማት ኮሚሽን በሚል እንደገና ተደራጀ፡፡ በዚህ ጊዜ የውሃ ልማት ባለስልጣን፣ የውሃ አቅርቦት እና ፍሳሽ ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 190/1980 ተቋቋሙ፡፡
3. የኢትዮጵያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ባለስልጣን የነበረው በ1994 ዓ.ም የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት (ው.ሥ.ኮ.ድ) በሚል ስያሜ በድጋሚ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ቁጥር 156/1986 ተቋቋመ፡፡ ይህ የማቋቋሚያ ደንብ በደንብ ቁጥር 109/1996 አማካኝነት ለድርጅቱ ተጨማሪ ኃላፊነት እና ተግባር ተሰጥቶት ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡ ማሻሻያው ተጠሪነቱ ለውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሲሰጥ የተፈቀደለት ካፒታልም ከሁለት መቶ አስራአንድ ሚሊዮን ሶስት ሺ ብር ወደ ሶስት ቢሊዮን ሰባት መቶ ዘጠኝ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማንያ ሺ ብር አድጓል፡፡ ድርጅቱ የመጠጥ ውሃ ፣ የግድብና መስኖ፣ የመንገድ፣ የደረቅ ወደብ ፣ የህንፃና ሌሎች የተለያዩ ግንባታዎችን ያካሂዳል፡፡

የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ሥልጣንና ተግባር

4. ድርጅቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 156/1986 እና የማሻሻያ ደንብ ቁጥር 109/1996 መሰረት የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባር ተሰቶታል፡-

- የውሃ ሀብትን ለማልማት የሚሰሩ የግድብ ስራዎች፣ የመስኖ ስራዎችን፣ የውሃ ኃይል ማመንጫ ግንባታዎችን የመጠጥ ውሃ ማከፋፈያ መስመሮችን፣ የቆሻሻ ማስወገጃ መስመሮች ስራዎችን፣ የድሬኔጅ ስራዎችን፣ የጥልቅ የውሃ ጉድጓድ ስራዎችን፣ የሪክላሜሽን ግንባታዎችን፣ የወንዝ መከለስ ግንባታዎችን፣ የመንገዶችና የሕንጻ ግንባታዎችን ማከናወን፤
- ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ስራዎችን ማካሔድ፤
- የውሃ ሀብትን ለመስኖ እርሻና ተጓዳኝ ስራዎች ልማት ለማዋል የሚያስችሉ ግድቦችን በባለቤትነት ይሰራል፣ ያስተዳድራል፣ ለግንባታ ያወጣውን ወጪ ከተጠቃሚዎች በመሰብሰብ ገንዘቡን ለተመሳሳይ ልማት ያውላል፤
- ቦንድ ያወጣል፣ ይሸጣል፣ በዋስትና ያስይዛል፤
- በተጓዳኝ ለስራው የሚየስፈልጉትን የተለያዩ ቧንቧዎችን ሊያመርትና ሊሸጥ ይችላል፡፡

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ

5. የክትትል ኦዲቱ ዓላማ በኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ 2005/2006 ዓ.ም በግዢ እና ንብረት አስተዳደር ላይ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች፤ እንዲሁም የኮንስትራክሽን ድርጅቱ የተሰጡትን ማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ በኦዲት ክትትሉ ወቅት በኦዲት ቡድኑ ተጠይቆ በቀረበው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት ያከናወነ መሆኑን ክትትል በማድረግ የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም መገምገም እንዲሁም እስካሁን ያልተቀረፉ ችግሮች ካሉ ምክንያቱን በማየትና በማጣራት ችግሮች እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ መስጠት ነው፡፡

የክትትል ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

6. የክትትል ኦዲቱ የሸፈነው ከ2002-2005 ያሉትን የአራት በጀት ዓመታት እና የ2006 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሥራ ክንውኖችን እንቅስቃሴ መሰረት ባደረገ በኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት በግዥና ንብረት አስተዳደር አፈፃፀም ላይ በተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ለተገኙ ግኝቶች/ግድፈቶች/ የማሻሻያ ሀሳብ የተሰጡ በመሆኑ እነዚህን ግኝቶች ለማሻሻል ኮንስትራክሽን ድርጅቱ የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቶ በወቅቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ያልላከ በመሆኑ የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦችና

የተዘጋጀው የድርጊት መርሃ ግብር መተግበራቸውና ችግሮቹ መቀረፋቸውን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

7. የክትትል ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ዋና መ/ቤት፣ በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት እና በናሙና በተመረጡ ከሰም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች በመገኘት ለሚመለከታቸው ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ ከድርጅቱ የግዥና የንብረት አስተዳደርና አፈጻጸም ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎችን በመከለስ እና ንብረቶችን ባሉበት ቦታ ተገኝቶ በአካል በማየት ኦዲቱ ያስገኘውን ጥቅም በመገምገም ነው፡፡

የክትትል ኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች (Standards of follow up Audit)

8. የክትትል ኦዲቱ የመመዘኛ መስፈርቶች ቀደም ሲል በ 2005/2006 ዓ.ም በግዥና ንብረት አስተዳደር አፈፃፀም ላይ በተከናወነው የክዋኔ ኦዲት በተገኙ ግኝቶች/ግድፈቶችን ለማስተካከል የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች (Audit recommendation) መሰረት በማድረግ የኮንስትራክሽን ድርጅቱ ባዘጋጀው የድርጊት መርሃ ግብር የመጡ ለውጦችን ማየት እና ችግሮች ያልተሻሻሉ (ያልተቀረፉ) ከሆኑ ምክንያቶቹን በመመርመር የክዋኔ ኦዲቱ ያስገኘውን ውጤት መፈተሽ ነው፡፡ የማሻሻያ ሀሳቡ በአባሪ 1 ላይ ተመልክቷል፡፡

ክፍል ሁለት

በክትትል ኦዲቱ የተገኙ ግኝቶች

የኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የግዥ ሂደትን በተመለከተ

9. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኙት ግኝቶች፤በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በተንዳሆ፣ ከስም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች፣

   - የግዥ ዕቅድ የማይዘጋጅ መሆኑ፣ አቅራቢዎች ትክክለኛ ብቸኛ አቅራቢ ስለመሆናቸው በጥናት ሳይረጋገጥ ግዥ አልፎ አልፎ ከተወሰኑ አቅራቢዎች የሚፈጸም መሆኑ፣ ከ2003 እስከ 2005 በጀት ዓመታት በፕሮጀክቱ የተፈጸሙ ግዢዎች አልፎ አልፎ ግዥዎች በመከፋፈል የሚፈጸሙ መሆኑን፣ ከሲሚንቶ፣ ብረት እና ነዳጅ በስተቀር በድርጅቱ በርካታ ለኮንስትራክሽን የሚያገለግሉ እቃዎች በጥቅል የማይገዙ መሆኑን፣በፕሮፎርማ መገዛት የሚገባቸው ግዥዎች አልፎ አልፎ ከተለያዩ ድርጅቶች ቢያንስ ከሶስት አቅራቢዎች ፕሮፎርማ ሳይሰበሰብ ከአንድ አቅራቢ ብቻ በተገኘ ፕሮፎርማ ግዥ የሚፈጸም መሆኑ፣ ከ2003 እስከ 2005 በጀት ዓመታት በተንዳሆ፣ በከስም ግድብና መስኖ ልማት እና በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ በፕሮጀክቶች የተፈጸሙ ግዢዎች አልፎ አልፎ ግዥዎች ከግዥ ጣሪያ በላይ እንደሚፈጸም መሆኑ የሚሉ ናቸው፡፡

10. በክትትል ኦዲቱ እንደታየው ድርጅቱ ለሚያከናውነው የዕቃ ወይም አገልግሎት ግዥ በ 2006 ዓ.ም እና በ 2007 ዓ.ም እቅድ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ያዋለ መሆኑን ከቀረቡ ማስረጃዎች በማረጋገጥ በክዋኔ ኦዲቱ የተሰጠው ማሻሻያ ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

11. በድርጅቱ የአቅርቦትና ንብረት አስተዳደር ዘርፍ 2007 ዓመታዊ ሪፖርት ላይ በተገለፀው መሰረት ድርጅቱ በጀት ዓመት ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 457,388,590.74/አራት መቶ ሀምሳ ሰባት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሰማኒያ ስምንት ሺ አምስት መቶ ዘጠና ከ 74/100 ሳንቲም የሆነ 196 ያህል የተለያዩ የኮንስትራክሽን

እቃዎችና መሳሪያዎች ግዥ ከተጠቃሚዎች በቀረበው የግዥ መጠየቂያ ሰነድ መሰረት ያከናወነ መሆኑ በሪፖርቱ ላይ የተቀመጠ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ብር 391,049,024.26/85%/ የሚያወጡ 47 ዙር ግዥዎች በግልፅ ጨረታ፣ ብር 52,029,410.21/11%/ የሚያወጡ 60 የቀጥታ ግዥዎች፣ ብር 11,826,572.10/8%/ የሚያወጡ 22 ግዥዎች በውስን ጨረታ እንዲሁም ብር 2,476,298.96/1%/ የሚያወጡ 75 የፕሮፎርማ ግዥዎች የተከናወኑ ሲሆን፤ በቀጥታ ግዥ ከተከናወኑ ውስጥ ብር 50,255,357.16/96%/ የሚያወጣ ግዥ መንግስታዊ የንግድ ድርጅት ከሆኑት METEC እና GIW በቀጥታ የተፈፀመ ሲሆን፤ በውስን ጨረታ ከተገዙት ውስጥ ብር 10,146,571.40/86%/ የሚያወጣ ፔቪንግ ብሎክ ግዥ ተፈፅሟል፡፡

12. ግዥዎች በጥቅል በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው እሩብ ዓመት መፈፀም ያለባቸው ቢሆንም በ 2007 ዓ.ም የቀጥታ ግዥና የዋጋ ማቅረቢያ /Proforma/ ስልቶች በከፍተኛ መጠን አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ ለዚህም ዋና ምክንያቶቹ አገልግሎቱን የሚጠይቁ ጠያቂ ክፍሎች የግዥ ጥያቄያቸውን እቅዱን መሰረት ባደረገ መልኩ በጥቅል ከማቅረብ ይልቅ በተለያዩ ጊዜያት በተናጠልና አስቸኳይ በሚል በማቅረባቸው እና ድርጅቱ ባጋጠመው ከፍተኛ የገንዘብ እጥረት ግዥዎችን ከጥቅል ይልቅ በተናጠል እንዲፈፀሙ ያስገደደ ሁኔታ የተከሰተ መሆኑ በ 2007 ዓ.ም የድርጅቱ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ተመልክቷል፡፡

13. እንዲሁም በ2007 በጀት አመት የሥራ አፈፃፀም በግዥ መመሪያው ከተቀመጠው የፕሮፎርማ ግዥ ጣሪያ ብር 132,000 በላይ የፕሮፎርማ ግዥዎች ፈፅሟል፡፡ ለማሳያ ያህል

ተ.ቁ	የዕቃው ዓይነት	PR. NO.	RR	የተገዛበት የብር መጠን
1	TYRE	1055138	2215	155,826.02
2	MF ROD 138	219385	53109	175,000
3	SHUTTER	215963	23052	333,244.80

14.በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ የተገኙት ግዢን በዕቅድ መምራትን በተመለከተ ግኝቶች ያልተስተካከሉ መሆኑ በክትትል ኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

15. ስለ ጉዳዩ ለግዥ ንዑስ ሥራ ሂደት ሥራ አስኪያጅ በክትትል ኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ድርጅቱ በ 2006 እና 2007 በጀት ዓመት እቅድ ውስጥ የግዥ ዓመታዊና የየሩብ ዓመቱ የግዥ እቅድ ተዘጋጅቶ በድርጅቱ የሂደት ምክር ቤትና የሥራ አመራር ቦርድ አቅርቦ አፀድቆ ሥራ ላይ ማዋሉን ገልፀው በ2007 ዓ.ም ለድንገተኛ ብልሽት የተጠየቁ የፕሮፎርማ ግዝዎች ብር 2,476,298.96/1%/ የሚያወጡ 75 የፕሮፎርማ ግዥዎች በሙሉ የድርጅቱ የግዥ መመሪያ ያስቀመጠውን በአንድ ጊዜ የመገበያያ ዋጋ ብር 132,000 ጣሪያ በጠበቀ መልኩ ግዥ መፈፀማቸውን ገልፀዋል፡፡

16.የግዥ የሥራ ሂደት ሥራአስኪያጅ ይህን ቢሉም ከጣራው በላይ ስለተገዙት ግዥዎች ምክንያትና አግባብነት እንዲሁም ከመመሪያው ውጭ ለመገበያየት የሚያስችል ፈቃድ /ውሳኔ/ ማቅረብ ባለመቻላቸው የተሰጠው መልስ አግባብነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

17. በመሆኑም ድርጅቱ የዕቃና አገልግሎት ግዥን ለመፈፀም በቅድሚያ የግዥ ዕቅድ የሚያዘጋጅ ቢሆንም ከድርጅቱ መመሪያ አንፃር ግዥዎችን በመጀመሪያ እሩብ ዓመት አካባቢ በጥቅል ባለመፈፀሙ ግዥዎች ተከፋፍለው በቁጥ ቁጥ እንዲገዙ በማድረግ በየወቅቱ ለሚከሰት የዋጋ ንረት ከማጋለጡም በላይ ድርጅቱ በጥቅል ግዥ ማግኘት የሚያስችለውን የሀብት ቁጠባ የጊዜ ጥቅም በማሳጣት የህዝብን ገንዘብ በቁጠባ ጥቅም ላይ እንዳይውል በማድረግ ለብልሹ አሰራር በር በመክፈት የቁጥጥር ስርዓቱ ውጤታማ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡

የቼክ ክፍያ አፈፃፀምን በተመለከተ

18.በክዋኔ ኦዲቱ የተገኘ ግኝት

❖ በድርጅቱ ተንዳሆ እና ከሰም ግድብና መስኖ ፕሮጀክቶች የእቃዎች ግዢ የሚፈፅሙት ከአዲስ አበባ ሲሆን ለሚፈጸሙአቸው ግዢዎች ለክፍያ ይረዳ ዘንድ የግዥ ማዘዣ ለአሸናፊዉ ድርጅት ሲላክ ኮፒዉ ለፋይናንስ የሚደርስ ቢሆንም ቼክ

የሚዘጋጀው ግን በአቅራቢው ድርጅት ስም ሳይሆን በግዢ ባለሙያዎች ስም በመሆኑ አንዳንድ ጊዜ እስከ ብር 400,000.00 በግዢ ባለሙያዎች ስም የሚዘጋጅ መሆኑን የሚል ነው፡፡

19.በክትትል ኦዲቱ እንደታየው በድርጅት ሥር ባለው የሞጆ ደረቅ ወደብ ፕሮጀክት አብዛኛውን ግዜ ቼክ በእቃ ግዥ ሰራተኛ ስም የሚዘጋጅ መሆኑ ና ጉዳዩም ማሻሻያ ያልተደረገበት መሆኑ ታውቋል፡፡

20. ስለ ጉዳዩ ለሞጆ ደረቅ ወደብ ፋይናንስ ንዑስ የሥራ ሂደት መሪ በክትትል ኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እንደ ብረታብረት ኢንጅነሪንግ ላሉት ድርጅቶች ክፍያውን በባንክ አካውንታቸው ገቢ የሚያደርጉ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ግለሰብ ጨረታ አሸናፊዎች በቼክ ለመቀበል ስለማይፈልጉ በዕቃ ግዥ ሰራተኛው ስም ቼክ የሚዘጋጅ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

21. ድርጅቱ ለሚፈፅማቸው ግዥዎች ክፍያው ባሸናፊው አቅራቢ ድርጅት ስም ወይም በተከፈተ ባንክ አካውንት ባለመፈፀሙ ለገቢ ስራው ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር አሰራሮችና ስርአቶች እንዳይተገበሩ የሚያደርግ እና ለብልሹ አሰራር በር የሚከፍት ይሆናል ፡፡

የማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች ኪራይ በተመለከተ

22.በክዋኔ ኦዲቱ የተገኘ ግኝት፤

- በተንዳሆ እና ከስም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች በኪራይ የሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች የሰሩበት ሰዓት ምዝገባ የሚከናወነው በሳይት ላይ በሚገኝ የቀን ሰራተኛ ሲሆን የኪራይ ገልባጭ መኪናዎች ምልልስ እና መሳሪያዎች የሰሩበት ሰዓት በብጣሽ ወረቀት ላይ የሚመዘገብ መሆኑ፤ እንዲሁም የኪራይ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች ላልሰሩበት 2437.33 ሰዓት በአማካይ የክፍያ ስሌት መሰረት ብር 4,387,194.00 በላይ ክፍያ እንደተፈጸመ በናሙና ተመርጠው ከታዩት የኪራይ ማሽነሪዎች ክፍያ ሰነድ የታወቀ መሆኑ፤
- ከዚህም በተጨማሪም የመሳሪያ ኪራይ እንደመጨረሻ አማራጭ ተወስዶ በቀን አንድ ገልባጭ መኪና ሊገዛ የሚችል ገንዘብ ለኪራይ ማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች ወጪ ከመደረጉ በፊት በድርጅቱ አስቀድሞ የአዋጭነት ጥናት /Cost Benefit Analysis/ እንዳልተሰራ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል የሚል ነው፡፡

23. በክትትል ኦዲቱ እንደታየው ድርጅቱ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ለመፈፀም የሚያስፈልጉትን የተሽከርካሪ እና የማሽነሪዎች የኪራይ ውሳኔ እና ወጪ ከማውጣቱ በፊት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በኪራይ ማቅረቡ አዋጭ መሆኑ በቅድሚያ የአዋጭነት ጥናት/Cost Benefit Analysis/ የሚሰራ ስለመሆኑ በክትትል ኦዲቱ ወቅት የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ ድርጅቱ የአዋጭነት ጥናትን በተመለከተ እንደማስረጃ ያቀረበው በትርፍ ላይ የተመሰረተ የቢዝነስ ተቋም መሆኑን የሚገልፅ በ 2005 ዓ.ም የተዘጋጀ በወቅቱ የመሳሪያ ግዥ፣የኪራይ መሳሪያዎችን የኪራይ ዋጋና በንግድ ሚኒስቴር በታህሳስ ወር የተመደበውን የነዳጅ ዋጋ መሰረት ያደረገ እንደገና ተሸሽሎ የተዘጋጀ የመሳሪያ ኪራይ የሰዓት ክፍያን በጥናት የተመሰረተ የግንባታ መሳሪያዎችን እስከ ነዳጅ አጠቃቀም ተመናቸው የሚያሳይ ማስረጃ ሲሆን ከላይ የተነሳውን ሃሳብ የሚመልስ ባለመሆኑ ማስረጃው የአዋጭነት ጥናት ነው ብሎ ለመቀበል አያስችልም፡፡በመሆኑም በዚህ ዙሪያ የተስተካከለ ነገር አለመኖሩ ተረጋግጧል፡፡

24. በተጨማሪም ከኪራይ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች ተገቢው አገልግሎት ስለመገኘቱ በቅርብ ኃላፊ ክትትል በማድረግ በየወሩ ሪፖርት ለዋና መ/ቤት ሊደርስ የሚችልበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ በናሙና ተመርጠው በታዩ በድርጅቱ ሥር ባሉ ከሰም መስኖ ግድብ ልማትና ሞጆ ደረቅ ወደብ ፕሮጀክት በመስክ ጉብኝት ማግኘት ከተቻሉት ናሙና ማስረጃዎች አንዱን ለማሳያ ለማቅረብ ድርጅቱ በኪራይ ውል ስምምነት 01/10/2007 ዓ.ም የተከራየው Cat. Dozer በሰዓት ብር 2660 ቫትን ጨምሮ የየዕለት ሥራው በሳይት ላይ በቅፅ በተዘጋጀ መቆጣጠሪያ በእያንዳንዱ ቀን ሥራ ጠዋት እና ከሰዓት በኋላ የጀመረበትና የጨረሰበት ሰዓት፣ እንዲሁም ያልተሰራባቸው ተሞልተው በሚመለከታቸው ኃላፊዎች ፊርማ ተረጋግጠው ለምህንድስና ክፍል የሚላክ ሲሆን፣ የምህንድስና ክፍሉ የደረሰውን ሪፖርት መሳሪያው በሥራ ላይ እያለ የተጠቀመውን የነዳጅና ቅባት ፍጆታ በእያንዳንዱ ቀን በማገናዘብና በመመዝገብ አጠቃላይ ወራዊ ሪፖርት ለፕሮጀክቱ ፋይናንስ ክፍል ሪፖርት የሚያደርግ መሆኑና፣ የፕሮጀክት ፋይናንስ ክፍልም በመሸኛ ደብዳቤ ማሽኑ የሰራወን ሪፖርት ለአከራዩ ክፍያ እንዲፈፀም ወደ ዋና መ/ቤት ኮርፖሬት ፋይናንስ የሚልክበት የአሰር ሂደት ያለ መሆኑ በመስክ ኦዲት ክትትል ከታዩና በማስረጃነት ከተሰበሰቡ ሰነዶች መረዳት ተችሏል፡፡ በዚህ ላይ የተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ ተግባራዊ መደረጉ ተረጋግጧል፡፡

25. ድርጅቱ ወደትግበራ ከመግባቱ በፊት የመሳሪያዎች ኪራይ ወጪ የተሻለ አማራጭ መሆኑን የሚያረጋግጥ ጥናት የሌለ በመሆኑ ከኪራይ በሚከፈለው ወጪ ከዚህ በተሻለ ዘዴ መገልገል ይችሉ እንደሆን አማራጭ እንዳያዩ ከማድረጉ በላይ በተደጋጋሚ የሚከናወን ስራ ላይ የሚውል ማሽን በአጭር ጊዜ በኪራዩ ድምር ወጪ ብቻ ሊገዛው የሚችልና ለተመሳሳይ ፕሮጀክቶችም ይህንኑ ማሽን መገልገል የሚችል በመሆኑ ባልተጠና አማራጮችን ባላገናዘበ መልኩ ለኪራይ የሚወጣው ገንዘብ እንደብክነትና የህዝብን ሃብት በቁጠባ ለመጠቀም ያለ ጥረትና ተነሳሽነት አናሳ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

በግዥ፣ በእርዳታ እና በስጦታ የሚያገኛቸው ንብረቶችን አመዘጋገብ በተመለከተ

26.በክዋኔ ኦዲቱ የተገኙ ግኝቶች

- ❖ በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በተንዳሆ፣ ከስም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች ንብረቶች ተገዝተው ገቢ ሲደረጉ በስፔስፊከሽኑ መሰረት ጥራቱን ጠብቀው መገዛታቸው በሚመለከተው ባለሙያ የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት አለመኖሩ፤፡
- ❖ በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት ማን (MAN) ለተባለ ገልባጭ መኪና ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ወጥቶ የተገዙት 12 የፊት እና 12 የኋላ በድምሩ 24 ባሌስትራዎች (Leaf Springs) ለመኪናው የማይሆን በመሆኑ ከሁለት ዓመት በላይ በግምጃ ቤት የተቀመጠ መሆኑን የሚሉ ናቸው፡፡

27. በክትትል ኦዲቱ እንደታየው በቃሊቲ እስቶር ንብረቶች ተገዝተው ገቢ ሲደረጉ በስፔስፊከሽኑ መሰረት ጥራቱን ጠብቀው መገዛታቸው ወይም በእርዳታና በስጦታ የተገኙ ስለመሆናቸው በሚመለከተው ባለሙያ የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት መኖሩ ና ተግባራዊ መደረጉ ተረጋግጧል፡፡ ለማሳያ ያህል በቀን 06/11/07 ዓ.ም ለንብረት አስተዳደር ንዑስ ሥራ ሂደት አስተዳደር ከኢንስፔክሽን ስፔስፊኬሽን ኬዝ ቲም ለዋናው መ/ቤት ህንፃ ለሰራተኞች ቢሮ አገልግሎት የሚውል የተለያዩ የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች ወደ ስቶር ገቢ ከመደረጋቸው በፊት የተሰራ የኢንስፔክሽን ሪፖርት 15 ዓይነት ዕቃዎችን የተለያየ የብዛት መጠን ያላቸውና በቀን 01/09/07 ዓ.ም ለDELL

Optipex 7010MT ኮምፒውተር ብዛታቸው 70 ለሆኑ መለዋወጫዎች/Accessories/ የኢንስፔክሽን ሥራ የተሰራባቸውን ሪፖርት ማስረጃዎች ማየት ተችሏል፡፡

28.ነገር ግን በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት እና በሞጆ ደረቅ ወደብ ፕሮጀክቶች ገቢ የሚሆኑ እቃዎችን በእስፔስፊኬሽን መሰረት የማይከታተሉ እና በባለሞያም የማይረጋገጡ መሆኑን ለማወቅ ተችላል፡፡ በነዚህ ፕሮጀክቶች በክዋኔ ኦዲቱ የተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ ተግባራዊ አለመደረጉን ታይቷል፡፡

29.ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኮንስትራክሽን ድርጅቱ ኃላፊዎች በክትትል ኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ፤

- የቃሊቲ ቅርንጫፍ ንብረት አስተዳደር ንዑስ የሥራ ሂደት ኃላፊ በሰጡት መልስ ንብረቶች በባለሙያ እንዲረጋገጡ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ በባለሙያ እየተረጋገጡ ገቢ የሚሆኑ መሆኑን ገልፀው ለአሰራሩ ማሳያነት ሁለት ማስረጃዎች በናሙናነት አቅርበዋል፡፡
- በከሰም ግድብ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የመሳሪያዎች አስተዳደርና ጥገና ንዑስ የሥራ ሂደት ኃላፊ ማን/MAN/ ለተባለ ገልባጭ መኪና 24 ባሌስትራዎች በእስፔስፊኬሽን መሰረት ባለመገዛታቸው ለተሽከርካሪው የማይሆኑ ከ 2 ዓመት በላይ በግምጃ ቤት መቀመጣቸው በወቅቱ በክዋኔ ኦዲቱ የተገኙ መሆኑን በተመለከተ በክትትል ኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የማን/MAN/ ገልባጭ መኪኖችን ባሌስትራ በተመለከተ ከዋናው መ/ቤት ቃሊቲ በ 2004 ዓ.ም የተላከ ሆኖ በወቅቱ ከማን/MAN/ ባሌስትራ ጋር የማይመሳሰል በመሆኑ በእስፔስፊኬሽን መሰረት ያለመሆኑን በደብዳቤ ለዋናው መ/ቤት የገለፁ መሆኑን፤ሆኖም ግን ወቅቱ በጣም የግድቡ ሥራ በአፋጣኝ የሚካሄድበት በመሆኑ እና በሀገር ውስጥም ትክክለኛውን ዕቃ የሚያስ መጣ ድርጅት የሌለ በመሆኑ ገጥማችሁ እዩትና ተጠቀሙ በሚል በቃል ትዕዛዝ ለመኪኖቹ በተለያየ ጊዜ ከንብረት ክፍል ወጪ በማድረግ ጥቅም ላይ ያዋሉ መሆኑን ገልፀው ለዚህም ማስረጃ ማን/MAN/ ገልባጭ መኪናዎች የጎን ታርጋ ቁጥር 533/1 ጊዜ/፣ የጎን ታርጋ ቁጥር 530/1 ጊዜ/፣ የጎን ታርጋ ቁጥር 535/3 ጊዜ/ ጥገና የተደረገላቸው መሆኑን የሚያሳይ 5 የጥገና መጠየቂያ ቅፆችን እና ለጥገና ለታርጋ ቁጥር 533 በእስቶር ኢሹ ስሊፕ ቁጥር 032992 የተጠየቁ በቁጥር 4 ባሌስትራዎች፣ ለታርጋ ቁጥር 530 በዕቃ መጠየቂያ ቁጥር 062111 የተጠየቀ በቁጥር 1ባሌስትራ እና ለታርጋ ቁጥር

535 በተለያዩ ቀናት በ 24/02/07 በእስቶር ኢ.ሹ ስሊፕ ቁጥር 075419 የተጠየቀ በቁጥር 1 ባሌስትራ እና በተመሳሳይ ቀን በእስቶር ኢ.ሹ ስሊፕ ቁጥር 075423 የተጠየቀ በቁጥር 1 ባሌስትራ፣ በእስቶር ኢ.ሹ ስሊፕ ቁጥር 075423 የተጠየቀ በቁጥር 1፣ በ 27/06/07 በ እስቶር ኢ.ሹ ስሊፕ ቁጥር 2322 የተጠየቀ በቁጥር 12 ባሌስትራእና በ 09/11/07 በእስቶር ኢ.ሹስሊፕ ቁጥር 455955 የተጠየቀ በቁጥር 1 ባሌስትራ፤እንዲሁም በእስቶር ኢ.ሹስሊፕ ቁጥር 455959 በቁጥር 1 የተጠየቀ ባሌስትራ በድምሩ 22 ባሌስትራዎች ሥራላይ መዋላቸው ከቀረቡት ማስረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡

- በተጨማሪም በወቅቱ የቀረቡት ባሌስትራዎች ለመኪኖቹ የማይመሳሰሉ መሆናቸው የሚገልፅ ደብዳቤ ለዋና መ/ቤት በቁጥር መ92/ነ2/592 በቀን 29/01/2005 ዓ.ም የተፃፈ ማስረጃ በዋቢነት ቀርቦ መመልከት ተችሏል፡
- በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ የፋይናንስ ንዑስ የሥራ ሂደት መሪ በሰጡት መልስ በድርጅቱ በተለይ ከብረታብረትና ኢንጅነሪንግ ብቸኛ አቅራቢ የሚገዙ የመለዋወጫ ዕቃዎች በአግባቡ በትክክል እስፔስፊኬሽን እየተጠየቀ በተሟላ ሁኔታ አይሰራም፡፡ ከመሳሪያዎች አስተዳደር ጥገና በኩል የሚሞላው የግዥ መጠየቂያ ድርጅቱ ከሚያውቀው የመለዋወጫ ስም ጋር ሊለያይ ስለሚችል በናሙናው መሰረት/As per Sample/ ተብሎ እየተጠየቀ ከግዥ መጠየቂያ ጋር ተገናዝቦ እንዳመቺነቱ የመለዋወጫ ግዥ የሚፈፀም መሆኑን ገልፀዋል፡፡

30. ድርጅቱ በቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት ንብረቶች በእስፔስፊኬሽናቸው መሰረት በባለሙያ እየተረጋገጡ ወደ እስቶር የሚገቡበትን ስርዓት በክዋኔ ኦዲቱ በተሰጠው ማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የተገበረ ቢሆንም አሰራሩን በፕሮጀክት ደረጃ ያልተገበረ በመሆኑ በፕሮጀክቶች የሚገዙ ዕቃዎች ጥራታቸውን ያልጠበቁና ለሚፈለገው ዓላማ ሊውሉ የማይችሉ ዕቃዎች በመግዛታቸው ድርጅቱን ለብክነትና ለኪሳራ ሊዳርጉ ይችላሉ፡፡

ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠን መቀመጡን በተመለከተ

31. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኙ ግኝቶች፤ በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በተንዳሆ፣ ከሰም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች፡-

- ❖ በንብረት መጋዘን ውስጥ እቃዎች እንደ እንቅስቃሴያቸው ፍጥነት፣ አዲስ፣ የሚያገለገሉ፣ የማያገለግሉ፣ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ፣ እንዲሁም እንደተፈጥሮ ባህሪያቸው እንዲያዙ እና እንዲቀመጡ ያልተደረገ መሆኑን፣
- ❖ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ በክምችት ሊያዙ የሚገባቸው ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያላቸው ንብረቶች ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠን /Minimum & maximum Stock Level/ እንዲኖራቸው ያልተደረገ መሆኑን የሚሉ ናቸው፡፡

32.በክትትል ኦዲቱ እንደታየው በድርጅቱ ስር በሚገኙ በናሙና በታዩ በአቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት እና በሞጆ ደረቅ ወደብ በክምችት የሚያዙ እና ከፍተኛ እና ዝቅተኛ እንቅስቃሴ ያላቸው ንብረቶች የዝቅተኛና ከፍተኛ መጠን መግለጫ ስርዓት የሌለው መሆኑ፤ በግዥ ትዕዛዝ መጠየቂያ ላይ መጠን/Re order level/ በሚል ቅፁ ላይ ዝቅተኛና ከፍተኛ መጠን የሚል ዝርዝር የተቀመጠ ቢሆንም የማይሞላ መሆኑ፤ በክትትል ኦዲቱ ታይቷል፡፡ በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ የተሰጡት ማሻሻያዎች ተግባራዊ አለመደረጋቸው ተረጋግጧል፡፡

33.በተጨማሪም የዕቃዎችን አያያዝና አቀማመጥን በተመለከተ በቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት በመጋዘን የሚገኙት ንብረቶች አቀማመጣቸው በተገቢው ሁኔታ መሆኑ በክትትል ኦዲቱ ታይቷል፡፡ ነገር ግን በመጋዘን ውስጥ መቀመጥ የማይችሉት ንብረቶች (አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡ) የተቀመጡት በተበታተነ ሁኔታ የሳር ዳዋ ለብሰው መመልከት ተችሏል፡፡ በከሰም ግድብ መስኖ ልማትና በሞጆ ደረቅ ወደቦች ያሉ መጋዘኖች በአግባቡ ያልተደራጁ መሆኑ በአካል እይታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

34.ይህን በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት ንብረት አስተዳደር ኃላፊ ለክትትል ኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ መልስ አልሰጡም ወይም ማስረጃ አላቀረቡም፤በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት የመሳሪያ አስተዳደርና ጥገና አገልግሎት ንዑስ የሥራ ኃላፊ በሰጡት መልስ ከዚህ በፊት በነበረው የግድቡ ሥራ ብዙ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች በፕሮጀክቱ ላይ የነበሩ ሲሆን ቀስ በቀስ ወደ ሌላ ፕሮጀክት መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች ሲሄዱ፤ መለዋወጫ አብሮ ባለመሄዱ በግምጃ ቤት ውስጥ የታየ መሆኑን፤ እንዲሁም ዋና ዋና ዕቃዎች ከዋናው መ/ቤት የሚላኩ ሲሆን፤ የተወሰኑ አላቂ ዕቃዎች በፕሮጀክት የሚያዙ

በመሆኑ ለሁሉም ባለው የገንዘብ ችግር አንፃር በእስቶር ውስጥ ባለው ስፋት መጠን ዝቅተኛ እና ከፍተኛ መለየት አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡

35.ድርጅቱ በተካሄደው የክዋኔ ኦዲቱ የስቶክ መጠን የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት አድርጎ ተግባራዊ ለማድረግ በተዘጋጀ የድርጊት መርሃ ግብር እንደሚከናወን ቢጠቀስም ያልተተገበረ መሆኑ በኦዲቱ የተገኘውን ዋጋ ለማየት የማያስችል መሆኑ እና በየጊዜው ለግንባታ የሚያስፈልጉ እንደ ሲሚንቶ፣ ብረት፣ ነዳጅ፣ መለዋወጫና ሌሎች ዕቃዎች በሚፈለጉበት ወቅት በተፈለገው መጠን በመጋዘን ውስጥ ሊገኙ ስለማይችሉ ሥራ ሊስተጓጎል ይችላል፡፡ በመጋዘን ውስጥ ሊቀመጡ የማይችሉ ንብረቶችን በከላላ ሊቀመጡ እንዲሁም የዕቃዎች አቀማመጥና አያያዝ እንደ ተፈጥሮ ባህሪቸው ካልሆነ ለብልሽት ሊዳረጉ የሚችሉ ሲሆን፤አዲስ የተገዙት እና አገልግሎት የሚሰጡት ከማያገለግሉት ጋር አብረው ቢቀመጡ በቀላሉ ንብረቶቹን ለማግኘት ካለመቻሉም በላይ ለብክነትና ለስርቆት ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡

ንብረቶች ገቢና ወጪ ሥርዓትን በተመለከተ

36.በክዋኔ ኦዲቱ የተገኙ ግኝቶች

- በተንዳሆ እና በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ሲሚንቶዎች፣ ብረቶች እና ሌሎች የግንባታ እቃዎች ከንብረት ክፍል በአንድ ፎርማን በጥቅል ወጪ ከተደረጉ በኋላ ሳይት ላይ ላሉት ለሌሎች ፎርማኖች የጠየቁትን ያህል ያለምንም መተማመኛ/ሰነድ የሚታደል ሲሆን ለፎርማኖች ስንት እንደታደለ እና ስንት እንደቀረ የማይታወቅ መሆኑ፣ ከመጋዘን በጥቅል ወጪ የተደረገው የሲሚንቶ፣ ብረት እና ለሎች የግንባታ እቃዎች ለታለመላቸው ዓላማ በትክክል የዋሉ መሆኑ የሚታወቅበት የአሰራር ሥርዓት አለመኖሩ፤
- በአቅርቦት ቁጥጥር ክፍል የሚያዘው የሲሚንቶና የቆርቆሮ ስቶክ ካርድ እና በንብረት ያዥ የሚያዘው ቢን ካርድ ባላንስ የሌላቸው መሆኑ፣ መጋዘን ውስጥ ግን ከ 320 በላይ ከረጢት ሲሚንቶ እና ከ 320 በላይ የቤት ክዳን ቆርቆሮዎች መገኘታቸው፣
- ሲሚንቶዎች እና ብረቶች በንብረት ወጪ ማድረጊያ /Stores Issue Slip/ የሚፈቅደው ኃላፊ ወጪ እንዲደረግ በፊርማው ሳያረጋግጥ ከንብረት ክፍል ወጪ የሚደረጉ መሆኑን፣

- ለሥራ ከንብረት ክፍል ወጪ የተደረጉት እና ወጪ ያልተደረጉ ባለ8፣ ባለ10፣ ባለ12፣ ባለ16፣ ባለ20 ፌሮ ብረቶች በጣም በተቀራረበ ቦታ መለየት በማይቻል ሁኔታ በአንድ ላይ እንዲቀመጡ የተደረገ መሆኑን፣
- ሳይት ላይ አሸዋ፣ ጠጠር እና ሲሚንቶ ወደ ማቡኪያ መኪና (concrete mixer) ሲገባ ሲሚንቶ በሚጨመርበት ወቅት የሲሚንቶ ከረጢት በመቀደድ ሲሚንቶው በመሬት ላይ በመፍሰስ የሚባከን መሆኑን፣ የሚሉ ናቸው፡፡

37.በክትትል ኦዲቱ እንደታየው የገቢና ወጪ ንብረቶች በተገቢው ሰነዶች ገቢና ወጪ የሚደረጉ፤እንዲሁም በሚመለከተው ኃላፊ ፊርማ የሚፀድቁ ስለመሆኑ በኦዲት ውጤት ክትትሉ በድርጅቱ ስር ባሉ በናሙና በተመረጡ በቃሊተ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በከሰም ግድብና መስኖ ልማትና በሞጆ ደረቅ ወደብ ፕሮጀክቶች ኦዲት ሲደረግ፡- በቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት ለማስረጃነት በናሙና በታየው የዕቃ መረከቢያ ሰነድ/Receiving Report/ ቁጥር 40217 ዕቃውን የተረከበው ፀሀፊ ብቻ ፊርማ የታየ ሲሆን፤ የዕቃ ግዥ ፈፃሚና የመጋዘን ሱፐር ቫይዘሩ ፊርማቸውን ቅፁ በሚጠይቀው መሰረት ተፈርሞ ያልተገኘ መሆኑ፤

- ይሁን እንጂ የዕቃ ወጪ ማድረጊያ በሆኑ ሁለት በታዩ ቅፆች የቫውቸር ቁጥር 003262 በ 10/10/07 እና የቫውቸር ቁጥር 003416 በ 27/09/07 ወደ ጊዳቦ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት የተላኩ ንብረቶች በተሟላ መልኩ በሚመለከታቸው ኃላፊዎች በፊርማ መረጋገጣቸው ማየት ተችሏል፡፡
- በከሰም ግድብ መስኖ ልማት ፕሮጀክት በተመሳሳይ ሁኔታ በዕቃ መረከቢያ ሰነድ ቁጥር 24840 የዕቃው ተረካቢ በሰነዱ ላይ ፈርሞ የተገኘ ሲሆን የመጋዘን ሱፐርቫይዘሩ አለመፈረሙ ሲታይ፤እንዲሁም ዕቃ ጥቅም ላይ ባለመዋሉ ወደ መጋዘን መመለሱን በሚያሳይ ቅፅ/Stores return Slip/ የመጋዘን ኃላፊው ፊርማ የተቀመጠ ሲሆን የመጋዘን ሱፐር ቫይዘሩ ፊርማ ማየት አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም በዕቃ ወጪ ማድረጊያ ቅፅ ቁጥር 216268 ለወጡ ዕቃዎች የመጋዘን ሱፐር ቫይዘሩ ቅፁ በሚጠይቀው መሰረት ፈርሞ አልተገኘም፡፡
- ከሞጆ ደረቅ ወደብ በናሙና በታዩ ሁለት የወጪ መመዝገቢያ ቅፆች ቁጥር 155815 እና ቁጥር 155822 ላይ የመጋዘን ኃላፊው የፈረመ ሲሆን የመጋዘን ሱፐር ቫይዘሩ አለመፈረሙን ከቅፆቹ ላይ መመልከት ተችሏል፡፡

- በሲሚንቶ መጋዘን ውስጥ ጥብቅ ቁጥጥር ባለመኖሩ ምክንያት በቁጥር 22 የሚሆኑ የሙገር ሲሚንቶ ከረጢቶች ፈንድተው የታዩ ሲሆን በከረጢት መቁጠር የማይቻል ሲሚንቶ በመጋዘኑ ውስጥ ፈሶ የታየ በመሆኑ በመጋዘኑ ውስጥ እንደ ገቢነት ለመያዝ በሚያስቸግር ሁኔታ መሆኑ ማየት ተችሏል፡፡በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳብ ተግባራዊ አለመደረጉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

38. ስለ ጉዳዩ በክትትል ኦዲቱ ወቅት የሚለከታቸው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ፡-
    - በድርጅቱ የቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት የቃሊቲ ንብረት አስተዳዳር ኃላፊ የንብረት ገቢ ሰነዶች ተሟልተው ተዘጋጅተው ወደ ንብረት ቁጥጥር የሚላኩ መሆኑን ሲገልፁ፣
    - በከሰም ግድብ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የመሳሪያዎች አስተዳደርና ጥገና ንዑስ የሥራ ሂደት ኃላፊ ንብረት ወጪና ገቢ የሚደረገው በድርጅቱ የአሰራር መመሪያ መሆኑን አመልክተዋል፡፡
    - በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክት የፋይናንስ ንዑስ የሥራ ሂደት መሪ በፕሮጀክቱ ንብረቶች ወጪና ገቢ ሲደረጉ የንብረት ገቢና ወጪ ሰነዶች በሚመለከታቸው ኃላፊዎች መፅደቅን በተመለከተ የሰጡት መልስ የለም፡፡

39. የድርጅቱ ኃላፊዎች በናሙና በታዩት በቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት የንብረት ገቢ ሰነዶች የሚሟሉ መሆኑን፣ በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት በድርጅቱ የአሰራር መመሪያ መሰረት ይሰራል ቢሉም፤እንዲሁም በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክት የተሰጠ መልስ ባይኖርም በናሙና በታዩት የገቢና የወጪ ቅፅ ሰነዶች ላይ የሚመለከተው የመጋዘን ሱፐር ቫይዘር በፊርማ ሳያረጋግጥ ዕቃዎች ገቢና ወጪ የሚደረጉ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

40. በድርጅቱ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች በንብረት መጋዘን ገቢና ወጪ ከመደረጋቸው በፊት የገቢና ወጪ ሰነዶች በሚመለከተው ኃላፊ ፊርማ ፀድቀው እንዲፈቀዱ ካልተደረገ ንብረቶች ለታቀደላቸው ዓላማ መዋላቸው ለማረጋገጥ ባለመቻል ለጥፋትና ለብክነት እንዲጋለጡ በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

የነዳጅ ታንከሮች ካሊብሬት መደረጋቸውን በተመለከተ

41. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኙት፡- ለመሳሪያዎች እና ለተሽከርካሪ ነዳጅ ከማደያ በሚቀዳበት ወቅት በነዳጅ ዘይትና ቅባት መጠየቂያ ቫውቸር (መተአ 013) የሚፈለገው የነዳጅ መጠን ተገልጾ ሳይጠየቅና ሳይፈቀድ በቅድሚያ ለመሳሪያዎች እና ለተሽከርካሪው ነዳጅ እንዲሞላ የሚደረግ መሆኑን፣ የነዳጅ ማጠራቀሚያ ታንከሮች ካልብሬት ያልተደረጉ ወይም ስልጣን በተሰጠው አካል የሚይዙት ትክክለኛ መጠን ያልተረጋገጠ መሆኑን፣ የሚሉ ናቸው፡፡

42. በክትትል ኦዲቱ ድርጅቱ የነዳጅ ታንከሮችን ካሊብሬት ስለማስደረጉና የነዳጅ የዘይት የቅባት መጠየቂያ ቅፆችን ሥራ ላይ ስለማዋሉ ሲፈተሽ፡-

- በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት የሚገኝ የነዳጅ ታንከር ካሊብሬት መደረጉን ከደረጃዎች መዳቢ ባለስልጣን በቀን 27/12/2005 ዓ.ም በተሰጠ ሰርተፊኬት ቁጥር 980068 ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን፣ የነዳጅ የዘይትና የቅባት መጠየቂያ ቅፅ እየተሰራበት ስለመሆኑ ቫውቸር ቁጥር 0864404ትን በማስረጃነት መመልከት ተችሏል፡፡
- በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት የነዳጅ ማጠራቀሚያ ታንከሮች ፕሮጀክቱ ሥራ ከጀመረ ከ 1997 ዓ.ም ጀምሮ ካሊብሬት ያልተደረጉ መሆኑ በክፍሉ ኃላፊ የተገለፀ ሲሆን፣የነዳጅ የዘይትና የቅባት መጠየቂያ ቅፅ እየተሰራበት መሆኑን ማየት ተችሏል፡፡
- በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክት የነዳጅ ማጠራቀሚያ ታንከሮችን በተመለከተ ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ከነሀሴ 2003 ዓ.ም ጀምሮ ካሊብሬት ተደርጎ የማያውቅ መሆኑን መረዳት የተቻለ ሲሆን፣ የዘይትና የቅባት መጠየቂያ ቫውቸር/መተአ 013/ ሥራ ላይ ስለመዋሉ ናፍጣ የተጠየቀበት በቀን 17/02/08 ቁጥር 0362070 ቫውቸር ታይቷል፡፡

በመሆኑም በቃሊቲ ቅርንጫፍ የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ሁሉም ተግባራዊ የተደረጉ፣ በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት እና በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክት የነዳጅ ማጠራቀሚያ ታንከሮችን ካሊብሬት ያልተደረጉ ሲሆን የዘይትና የቅባት መጠየቂያ ቫውቸር/መተአ 013/ ሥራ ላይ ስለመዋሉ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

43. ስለ ጉዳዩ በክትትል ኦዲቱ ወቅት የሚለከታቸው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ፡-

- በከሰም ግድብ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የመሳሪያዎች አስተዳደርና ጥገና ንዑስ የሥራ ሂደት ኃላፊ የነዳጅ ታንከር ካሊብሬት መደረግን በተመለከተ ድርጅቱ ሥራ ከጀመረ ከ 1997 ዓ.ም ጀምሮ ካሊብሬት ያልተደረገ መሆኑን ገልፀው የነዳጅ ዘይትና ቅባት አጠቃቀምን በተመለከተ በመተአ/013/ ቅፅ እየተሰራ መሆኑን አስረድተዋል፡፡
- በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክት የነዳጅ ታንከር ካሊብሬት ለማስደረግ ለዋናው መ/ቤት የሬድዮ መልክት አስተላልፈው እየተጠባበቁ መሆኑን ሲገልፁ የነዳጅ ዘይትና ቅባት አጠቃቀምን በተመለከተ በመተአ/013/ ቅፅ እየተሰራ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

44. በድርጅቱ የነዳጅ ማጠራቀሚያ ታንከሮች ስልጣን በተሰጠው አካል የሚይዙት ትክክለኛ መጠን ካልታወቀና ካልተረጋገጠ በዚህ ክፍተት በመጠቀም ነዳጁ ለብክነት እና ለስርቆት ተጋላጭ ይሆናል፡፡

ቋሚ እቃዎች የሚሰጡት አገልግሎት በየጊዜው እየተገመገመ እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን በተመለከ

45. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኘው፡-በተንዳሆ እና በከስም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ከብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን (ብኢኮ) የተገዙት የድርጅቱ ስድስት FAW ገልባጭ መኪናዎች እና አምስት SHANTUI ዶዘሮች አንድ ዓመት ሳያገለግሉ ተበላሽተው የቆሙ መሆናቸውን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከዚሁ ድርጅት በተጨማሪ ለመግዛት ውል የተገባባቸው መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች ላይ ተመሳሳይ ችግር እንዳይከሰት በድርጅቱ እየተወሰደ ያለ እርምጃ ያለመኖሩ የሚሉ ናቸው፡፡

46. በክትትል ኦዲቱ እንደታዩት፡
    - በተንዳሆና በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ከብረታብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን የተገዙት የድርጅቱ ስድስት FAW ገልባጭ መኪናዎችና አምስት SHANTU ዶዘሮች አንድ ዓመት ሳያገለግሉ በመለዋወጫ ችግር ምክንያት የቆሙ ስለመሆናቸው፡-

- በአሁኑ ወቅትም ከቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት ጋራዥ መረዳት የተቻለው የSHANTU ዶዘሮች መለዋወጫ በግዥ ሂደት ላይ መሆኑን፤
- በከሰም ግድብ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የSHANTU ዶዘሮች የመለዋወጫ ችግር መፍትሄ ባለመገኘቱ ወደ ቃሊቲ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት የተላኩ መሆኑን ከስቶር ትራንስፌር ሺፒንግ ዶክመንት ቁጥር 088383፣ 088387 እና088389 ማስረጃዎች የታየ መሆኑን፣
- የFAW ገልባጭ መኪናዎችን በተመለከተ ሥራ ላይ ካልዋሉ የገልባጭ መኪኖች ሊስት በቀን 26/12/07 ማየት እንደተቻለው ብዛታቸው በቁጥር 6 የሆኑ ገልባጭ መኪናዎች በብልሽት ምክንያት በመለዋወጫ እጦት ሥራ ላይ ያልዋሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ የታዩት ችግሮች አሁንም ያልተሸሻሻሉና እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

47. ስለ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ፡-
    - የቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤትና የጥገና ጋራዥ ኃላፊዎቹ በሰጡት መልስ SHANTU ዶዘሮች መሥራት ከሚገባቸው ባነሰ ሰዓት ከፍተኛ ጥገና የፈለጉ ሲሆን መሳሪያዎቹ ከገቡበት መከላከያና ሌሎች ድርጅቶች መለዋወጫ በወቅቱ መቅረብ ባለመቻሉ ለረጅም ጊዜ በብልሽት ምክንያት መቆማቸውን ሆኖም መለዋወጫ በግዥ ሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑን፤ የFAW ገልባጭ መኪናዎችን በተመለከተ ሌሎች የመለዋወጫ ማቅረብ ስልቶችን በማየት በመግዛት ላይ የሚገኙ መሆኑን የገለፁ ቢሆንም የግዥ ሂደቱን የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፡፡
48. የከሰም ግድብ መስኖ ልማትና ፕሮጀክት የመሳሪያ አስተዳደርና ጥገና ንዑስ የሥራ ሂደት መሪ በሰጡት መልስ ከዚህ በፊት ፕሮጀክቱ ላይ የFAW ገልባጭ መኪና እና የSHANTU ዶዘሮች መለዋወጫ ችግር በመኖሩ ያለ ሥራ የቆሙ መሆኑ፤ ሆኖም ግን የSHANTU ዶዘሮች መለዋወጫ መፍትሄ እንዲያገኝ ወደ ቃሊቲ ማዕከላዊ መጋዘን ተልከው የሚገኙ ሲሆን፤የFAW ገልባጭ መኪና ሁኔታን በተመለከተ ግን ከብረታብረትና ኢንጅነሪንግ የመለዋወጫ ዕቃ የተገኘ በመሆኑ በፕሮጀክት ላይ ያሉት ሥራ እየሰሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የFAW ገልባጭ መኪናዎች ከታየው የቀን ውሎ ማስረጃ በብልሽት

ምክንያት ሥራ ያልሰሩባቸው ቀናት የበዙ በመሆኑ በኃላፊው የተሰጠውን መልስ መቀበል ያስቸግራል፡፡

49. ድርጅቱ አስፈላጊ የሆኑ መለዋወጫ የሌላቸው መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች በመግዛቱ ምክንያት መሳሪያዎቹና ተሽከርካሪዎቹ ያለ ሥራ በመቆማቸው ምክንያት ድርጅቱ በሥራ ምክንያት ማግኘት የሚገባውን ጥቅም በማጣት ለተጨማሪ ወጪና ኪሳራ እንዲዳረግ አድርጓል፡፡

የተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች ጥገና ሥርዓትን በተመለከተ

50. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኙ ግኝቶች ለጥገና ጋራዥ ገብተው በወቅቱ ተጠግነው ያልወጡ በቃሊቲ ጋራዥ 383፣ በተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት በተለያዩ ካምፖች በሚገኙ ጋራዦች 51 እና በከሰም ግድብ እና መስኖ ልማት ፕሮጀክት በተለያዩ ካምፖች በሚገኙ ጋራዦች 35 በጠቅላላው 469 የሆኑ የድርጅቱ ዶዘሮች፣ ኤክስካቫተሮች፣ ግሬደሮች፣ ሎደሮች፣ ገልባጭ መኪናዎች፣ ኮምፓክተሮች፣ ደብል ካፕ መኪናዎች እና የተለያዩ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች ከአራት ወራት በላይ የሆናቸው መኖራቸው፣

- በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት በየወሩ ከ175 በላይ የሚሆኑ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች ለጥገና ጋራዥ የሚገቡ ቢሆንም የጥገና ታሪክ /History Jacket/ የሌላቸው፣ ከመጠገናቸው በፊት የብልሽታቸው መንስኤ ስለመጣራቱ እና ተጠግነው ከወጡ በኃላም በትክክል ስለመጠገናቸው በኢንስፔክሽን ስለመረጋገጡ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑን፣
- በተንዳሆና ከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ለጥገና ጋራዥ የሚገቡ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች የተሽከርካሪዎች ጥገና መጠየቂያ፣ የጥገና ሥራ ትዕዛዝ እና የተቀየሩ የመለዋወጫ እቃ ቅጾች በሚመለከታቸው ባለሙያዎች እና ኃላፊዎች የማይሞሉ እና የማይፈረሙ መሆኑ፣
- እንዲሁም ለጥገና ጋራዥ የሚገቡ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች በትክክል ስለመጠገናቸው እና ተቀይረዋል የተባሉ መለዋወጫ ዕቃዎች በትክክል መቀየራቸው የሚረጋገጥበት የአሰራር ስርዓት አለመኖሩን፤ የሚሉ ናቸው፡፡

51. በክትትል ኦዲቱ በታዩት፡-

- በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት የተሽከርካሪዎችና መሳሪያዎች ጥገና ቅፅ፣የሾፕ የሥራ ጥገና ትዕዛዝ፣ከመጋዘን ዕቃ ወጪ ማድረጊያ/Stores Issue Slip/ ቁጥር 083803፣የብልሽት ሁኔታ በቅድሚያ የኢንስፔክሽን ሥራ የሚሰራበት የተሽከርካሪ ኢንስፔክሽን ቼክ ሊስት ለማሳያ ስካንያ የሰሌዳ ቁጥር 3-16315 የታየበት ከተሰራም በኋላ በትክክል ስለመሰራቱ በኢንስፔክሽንና እስፔስፊኬሽን ኬዝ ቲም የሚረጋገጥ ስለመሆኑ በናሙና ከታየ ጥገና የተከናወነለት የስካንያ ትራክ የሰሌዳ ቁጥር 3-14056 ማስረከቢያ ቅፅ ማስረጃዎች መረዳት የተቻለ ሲሆን፤
- በከሰም ግድብ መስኖ ልማት እና በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች የጥገና መጠየቂያ፣ የሥራ ትዕዛዝ ቅፆች እና ዕቃ ወጪ ማድረጊያ ሥራ ላይ የዋሉ ቢሆንም በፕሮጀክት ደረጃ የኢንስፔክሽን ሥራ የማይሰራ መሆኑ ታውቋል፡፡ በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች በቃሊቲ ቅርንጫፍ ተሻሽሎ የታየ ሲሆን በከሰም ግድብ መስኖ ልማት እና በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክት ያልተስተካከለ መሆኑ ታውቋል፡፡

52. ስለጉዳዩ ለከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት ለመሳሪዎችና ጥገና ንዑስ የሥራ ሂደት ኃላፊ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ በአወቃቀር ደረጃ በፕሮጀክቱ የኢንስፔክሽን አካል የሌለ ቢሆንም የጥገና ባለሙያ ብልሽቱን አረጋግጦ ሥራ የሚጀምር መሆኑን፤ በትክክል ስለመሰራቱም ተጠቃሚው አረጋግጦ የሚረክበት ሁኔታ ያለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክት የፋይናንስ ንዑስ የሥራ ሂደት ኃላፊ በሰጡት መልስ በመዋቅር ደረጃ ለዚህ ጉዳይ የተመደበ አካል የሌለ መሆኑንና ሆኖም ግን ከፍተኛ መካኒክ ምትክ በመሆን የሚሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

53. ድርጅቱ በቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት ያደራጀውን የኢንስፔክሽንና እስፔስፊኬሽን ኬዝ ቲም በፕሮጀክት ደረጃ አለማዋቀሩ በፕሮጀክት ደረጃ ተጠግነው ቶሎ ወደተግባር እንዳይሸገሩ ከማድረጉም በላይ በጋራዦች የሚደረጉ የጥገና ሥራዎች የቁጥጥርና ክትትል ትኩረት እንዳይኖረው ከማድረጉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር እንዲከፈት ያደርጋል፡፡

አገልግሎት የማይሰጡ መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎችና መለዋወጫዎችን በተመለከተ

54. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኙ ግኝቶች፡- በተንዳሆ፣ ከሰም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች ከአገልግሎት የተመለሱ ንብረት ክፍል ተመላሽ መደረግ የነበረባቸው የተለያዩ ውፍረት ያላቸው በርካታ ባለ 8፣ ባለ 10፣ ባለ 14፣ ባለ 16፣ ባለ 20፣ ባለ 30 እና ባለ 32 ፌሮ ብረቶች በየፕሮጀክቶቹ ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ ተከማችተው የተቀመጡ መሆኑ፤

55. ከዚህም በተጨማሪ በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርጫፍ መ/ቤት ውስጥ ብዛት ያላቸው ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ 185 ዶዘሮች፣ ግሬደሮች፣ ኤክስካቫተሮች፣ ኮምፓክተሮች፣ ገልባጭ መኪናዎች፣ ደብል ካፕ መኪናዎች፣ ለግንባታ ስራ የሚያገለግሉ የተለያዩ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች እንዲሁም ጄነሬተሮች፣ ኮምፕረሰሮች፣ መበየጃ ማሽኖች፣ ለጥልቅ ውሃ ጉድጓድ የሚያገለግሉ ዕቃዎች፣ የሲሚንቶ ማቡኪያ ሚክሰሮች፣ ሲሚንቶ መጠቅጠቅያ፣ መሬት መጠቅጠቅያ፣ የተለያዩ መጠን ያላቸው ዲናሞዎች እና ለግንባታ ሰራ የሚያገለግሉ በርካታ የኮንስትራክሽን መሳሪያ አካላትና እቃዎች፣ ለድርጅቱ አገልግሎት የማይስጡ መለዋወጫዎች እና ከአገልግሎት የተመለሱ አሮጌ መለዋወጫዎች መጋዘን አጣበው ፣ በቃሊቲ ግቢ ውስጥ የሚገኙ መሆኑን፣ የሚሉ ናቸው፡፡

56. በክትትል ኦዲቱ እንደታየው ድርጅቱ አገልግሎት ላይ የማይውሉ መሳሪያዎችን፣ተሽከርካሪዎችንና መለዋወጫዎችን በድርጅቱ አወጋገድ መመሪያ እንዲያስወግድ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት መተግበር መጀመሩን የሚያሳይ በጥር 27/ 2007 ዓ/ም አሸናፊ ተወዳዳሪዎችን ካሳወቀበት ማስታወቂያ በዝርዝር ያገለገሉ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎችን፣ ቀላልና ከባድ ተሽከርካሪዎችን፣የውሃ ፓምፖችና ጀነሮተሮችን ሽያጭ ታህሳስ 5/2007 ዓ.ም በወጣ ጨረታ የተሸጡ ብዛት 81 የሆኑ በብር 3,487,692.98 መገንዘብ ተችሏል‹‹ በተጨማሪም በ 2008 ዓ.ም በቁጥር 173 የሆኑ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎችን ለመሸጥ የተቃደ መሆኑን ከድርጅቱ ከቀረበ ማስረጃ መመልከት ተችሏል፡፡

57. ድርጅቱ በክዋኔ ኦዲቱ የተሰውን የማሻሻያ ሀሳብ ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩ ድርጅቱ የቦታ ጥበት ችግርን ከማቃለሉም በላይ ንብረቶቹን ለብልሽትና ለብክነት ሳይጋለጡ በፊት በማስወገድ ሌላ አካል እንዲጠቀም የሚያስችል እና ድርጅቱም በሽያጩ የገንዘብ ተጠቃሚ እንዲሆን ስለሚያስችል ሊበረታታ የሚገባው አሰራር ነው፡፡

የነዳጅ አጠቃቀምና የስምሪት መመሪያ በተመለከተ

58. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኙ ግኝቶች፡- በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት አገልግሎት መስጠት እየቻሉ በኦፕሬተር እጥረት ምክንያት አንድ ቮልቮ ሎደር፣ ሁለት ኮምፓክተሮች ያለስራ ከአንድ ወር በላይ የቆሙ መሆናቸው፤ በተንዳሆ፣ ከስም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች የድርጅቱ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች መስራት ከሚገባቸው ሰዓት /Potential Hour/ በታች እየሰሩ እንደሚገኙ እና የዕለት፣ የሳምንት፣ የወር የስምሪት ሪፖርት የማይዘጋጅላቸው መሆኑን የሚሉ ናቸው፡፡

59. በክትትል ኦዲቱ እንደታየው ድርጅቱ የነዳጅ አጠቃቀምና የስምሪት መመሪያ በተመለከተ በቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት ለተሽከርካሪዎች ለሎውቤድ፣ሀይ ቤድ፣ለተሳቢ፣ለካርጎ፣ለክሬን፣ ኒሳንና እስካን ለመሳሰሉት እቃ ጭነውም ሆነ በባዶ ሲመለሱ በአንድ ሊትር ምን ያህል ኪሎሜትር እንደሚጓዙ የሚያሳይ የነዳጅ አጠቃቀምና የስምሪት መመሪያ ያለው ሲሆን፣ የማሽነሪና የግንባታ መሳሪያዎችን በነዳጅ፣ ዘይትና ቅባት መጠየቂያ ቫውቸር/መተአ 013/ መቆጣጠሪያ ቅፅ የሚከታተል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

60. በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት የተሽከርካሪ፤ የማሽነሪ እና የግንባታ መሳሪያዎች የነዳጅ አጠቃቀም በነዳጅ፣ በዘይትና ቅባት መጠየቂያ ቫውቸር/መተአ 013/ መቆጣሪያ ቅፅ ክትትል የሚደረግ መሆኑ ከቅፆች መመልከት የተቻለ ሲሆን የድርጅቱ መሳሪዎች በሥራ ላይ በቀን ውሎ ስለመዋላቸውም ሆነ አለመዋላቸው በተዘጋጀ ቅፅ በስምሪት ክፍል ክትትል የሚደረግ መሆኑ በቀን 27/12/07 በተዘጋጀ የድርጅቱ ማሽኖች ውሎ ዝርዝር ከሚያሳይ በናሙና ከተወሰደ ቅፅ መረዳት የተቻለ ሲሆን፤የኪራይ መሳሪያዎችን በተመለከተ ለማሳያ ካት ዶዘር 628 የሆነ መሳሪያ በሰኔ ወር ውስጥ ለሰራባቸው 16 የሥራ ቀናት ጠዋት እና ከሰዓት በኋላ ሥራ የጀመረበትና ያቆመበት ሰዓት እንዲሁም በሥራ የሸፈናቸው ሰዓቶች እና በሥራው ወቅት የተጠቀመው ነዳጅ፣ዘይትና ቅባት ተመዝግቦ የሚያዝ መሆኑን ከቀረበው ሰነድ ማወቅ ተችሏል፡፡

61. በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክትም በተመሳሳይ ሁኔታ በናሙና ከታየ ከነሀሴ ወር 2007 ዓ.ም የኪራይ ግንባታ መሳሪያ HYUNDIA EXCAVATOR የመለያ ቁጥር EX-1025 በወር ውስጥ የተሰማራባቸው የሥራ ሰዓቶች ተመዝግበው መታየቱ የስምሪት

ክትትል የሚሰራ መሆኑን፣ እንዲሁም በተጓዳኝ የሚጠቀመውም የነዳጅ መጠን የሚረጋገጥ መሆኑ ታውቋል፡፡

62. በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ማድረግ መጀመራቸው የተረጋገጠ ሲሆን ድርጅቱ የግንባታ መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎችን የሥራ ስምሪትና የነዳጅ፣የቅባትና የዘይት ቁጥጥርና ክትትል ስርዓት መተግበሩ ድርጅቱ ለሚያወጣው ወጪ ተመጣጣኝ የሆነ ግብዓት እንዲያገኝ ያስችለዋል፡፡

ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ/Inventory/ በተመለከተ

63. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኘው፡- በተንዳሆ እና ከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ባለፉት ሶስት ዓመታት አመታዊ የንብረት ቆጠራ የሚደረግ እና ከንብረት መዛግብት ጋር የሚመዛዘን ቢሆንም በየአመቱ በተደረገው ቆጠራ በመብለጥና በማነስ የታዩት ልዩነቶች ለሚመለከተው ኃላፊ ቀርበው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያልተደረገ መሆኑ የሚል ነው፡፡

64. በክትትል ኦዲቱ በታየው በከሰም ግድብ መስኖ ልማት ፕሮጀክት በ 2006 ዓ.ም ከተደረገ የንብረት ቆጠራ በናሙና ከተወሰደ 10 የዕቃ ዝርዝሮችን ከያዘ 8 የመብለጥና 2 ማነስ ከታየበት ማስረጃ ለማሳያ ያህል በሊትር መጠን ብዛት 4,66 ከፍተኛ መብለጥ ያሳየ Oil No.140 በካርድ የተመዘገበ 2,803 ሊትር ሲሆን በቆጠራ ወቅት የተገኘ 3,269 ሊትር የሆነ፣እንዲሁም በማነስ Oil No.90 መለኪያ ሊትር የሆነ በካርድ የተመዘገበ 4,245 ሊትር ሲሆን፣ በቆጠራ የተገኘ 4,101 ሊትር ልየነት 144 ሊትር በማነስ የታየበት በሚመለከተው አካል የተሰጠ የማስተካከያ እርምጃ የሚያሳይ መረጃ ቀርቦ መመልከት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ የተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ በከሰም ግድብ መስኖ ፕሮጀክት ያልተተገበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

65. ስለሁኔታው ጉዳዩ የሚመለከታቸው በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት የፋይናንስ ንዑስ የሥራ ሂደት ኃላፊ በክትትል ኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በድርጅቱ መመሪያ መሰረት ቆጠራ በየዓመቱ በሚካሄድበት ወቅት በማነስና በመብለጥ የሚታዩ ልዩነቶች የዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ማስተካከያ ሪፖርት ተሞልቶ በመፈራረም ከቆጠራ ሰነድ ጋር ወደ ዋናው መ/ቤት ኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ከቆጠራ ሰነድ ጋር የሚላክ መሆኑን ቢገልፁም ሆኖም ግን በዚህ ጉዳይ ለቀረበ ጥያቄ በዋናው መ/ቤት በኩል የተሰጠ መልስ የለም፡፡

66. ድርጅቱ በስሩ ላሉ በፕሮጀክት ደረጃ ለሚደረግ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ የሚታይ የማነስ ወይም የመብለጥ ሁኔታ በሚቀርብለት ሪፖርትና የቆጠራ ሰነድ አማካኝነት ወቅታዊ የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰዱ የንብረት አያያዝ ስርዓቱ እንዳይዳብር ከማድረጉ በላይ በንብረት ላይ ብክነትና ስረቆት እንዲፈፀም በር ከፋች ይሆናል፡፡

የመረጃዎች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መያዛቸውን በተመለከተ

67. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኘው ፡- በቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት፣ በተንዳሆ፣ ከሰም ግድብና መስኖ ልማት እና ሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መረጃዎች በዘመናዊ ተክኖሎጂ ተደግፈው ያልተደራጁ መሆኑን የሚል ነው፡፡

68. በክትትል ኦዲቱ እንደታየው በድርጅቱ ቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት በዳታ ቤዝ ሥራውን ለመጀመር ከሀምሌ 15/2007 ዓ.ም ጀምሮ በእንቅስቃሴ ላይ መሆናቸውን፣ በከሰም ግድብ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ዳታ ቤዝ እንዲሰራ ባለሙያ እየጠበቁ ያሉ መሆኑን፣ በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክት በዳታ ቤዝ አሰራር ለመስራት ከዋናው መ/ቤት ጋር አስፈላጊው ጥረት እየተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

69. ስለ ጉዳዩ በዋናው መ/ቤት የግዥ ነዑስ ሥራ ሂደት ሥራ አስኪያጅ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ በአሁኑ ሰዓት የድርጅቱ ዌብ ሳይት ተዘጋጅቶ የተለቀቀ ሲሆን ለግዥ ክፍል አስፈላጊ የሆኑ ዳታ ቤዞች በመዘጋጀት ላይ ያሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

70. በድርጅቱ የዋናው መ/ቤት የግዥ ንዑስ ሥራ ሂደት ሥራ አስኪያጅ ይህን ይበሉ እንጂ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም በኩል የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ እስከ ክትትል ኦዲቱ መጠናቀቂያ ወቅት ድረስ ተግባራዊ አለማድረጋቸው የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

71. ድርጅቱ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መረጃዎች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ካልተደገፉ የሚፈለጉ መረጃዎችን በወቅቱ በጥራት ለማግኘት፣ለመጠቀምና ለመለዋወጥ አያስችልም፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በክዋኔ ኦዲቱ ያስገኘው ጥቅም በተመለከተ

72. በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በግዥና ንብረት አስተዳደር ላይ የክዋኔ ኦዲት በ 2005/2006 ዓ.ም በመከናወኑ ለድርጅቱ ያስገኘውን ፋይዳዎች ውስጥ፣

- ግዥዎች ከመፈፀማቸው በፊት የግዥ እቅድ እንዲዘጋጅ እና በእቅዱ መሰረት እንዲፈፀም መደረጉ፣
- የድርጅቱ የነዳጅ አቅርቦትና ስርጭት ችግሮችን እንዲቀረፉ መደረጉ፣
- የግዥ ባለሙያዎች ግልፀኝነትና ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ እንዲሰሩ መደረጉ፣
- የተሽከርካሪዎችና የግንባታ መሳሪያዎች ኪራይ ላይ የነበረውን ክፍተት ለመቅረፍ መቻሉ ከተከለሱ ሪፖርቶችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ክፍል ሶስት

መደምደሚያ

የኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ወጪ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የሆነ የግዥና ንብረት አስተዳደር ሥራዎችን ለማከናወን ማነቆ የሆኑ የአሰራር ድክመቶች ያሉበት መሆኑ በ 2005/2006 ዓ.ም በተደረገው የክዋኔ ኦዲት ከተገለፁት በአንፃራዊ ሁኔታ ሲታይ በተሻለ መልኩ የተቀረፉ ቢሆንም በክትትል ኦዲት ወቅትም አፅንዖት ተሰጧቸው መወገድ የሚገባቸው ችግሮች ያሉ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡እነርሱም ዋናዋናዎቹ፡-

73. ድርጅቱ በ 2006 ዓ.ም እና በ 2007 ዓ.ም የግዥ እቅድ አዘጋጅቶ ግዥዎችን የፈፀመ ቢሆንም በድርጅቱ የግዥ ጠያቂ ክፍሎች የግዥ ጥያቄን በጥቅል ከማቅረብ ይልቅ በተለያዩ ግዜያት ለአስቸኳይ ሁኔታ በማለት በተናጠል ጥያቄ በማቅረባቸው የዋጋ ማቅረቢያ/Proforma/ግዥ ስልት አሁንም በስፋት በሥራ ላይ የሚገኝ መሆኑ፤ እንዲሁም ድርጅቱ ካስቀመጠው የዋጋ ማቅረቢያ/ Proforma/ ግዥ ከ ብር 132000 ጣሪያ በላይ ግዥ ተፈፅሞ የተገኘ መሆኑ፡
74. በድርጅቱ ሥር ባለው የሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክት ግዥ ሲፈፀም ክፍያው ባሸናፊው አቅራቢ ድርጅት ስም ወደተከፈተ የባንክ ሂሳብ መግባት ሲገባው በግዥ ባለሙያዎች ስም ቼክ የሚዘጋጅ መሆኑ፣
75. ድርጅቱ ለማሽነሪዎች ኪራይ የሚያወጣው ወጪ አዋጭ መሆኑ በቅድሚያ የአዋጭነት ጥናት /Cost Benefit Analysis/ ሰርቶ የሚያረጋግጥ መሆኑ፣
76. በከሰም ግድብ መስኖ ልማት እና በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ወደ ድርጅቱ መጋዘን ከመግባታቸው በፊት በእስፔስፊኬሽናቸው መሰረት ስለመሆናቸው የሚከታተል አካል የሌለ መሆኑ፣
77. በድርጅቱ የእስቶክ ቁጥጥር አሰራር ላይ የዕቃዎች የዝቅተኛና የከፍተኛ ክምችት/MIinimum & Maximum Stock Level/ መጠን ያልተቀመጠ መሆኑ፣
78. ንብረቶች ገቢና ወጪ ሲደረጉ የሰነድ ስርዓት መሟላቱን በተመለከተ በቃሊቲ ቅርንጫፍ መ/ቤት በዕቃ መረከቢያ ሰነድ፣ በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት በዕቃ

መረከቢያና ወጪ ማድረጊያ ሰነድ፣ በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክት የወጪ መመዝገቢያ ሰነድ በሚመለከታቸው የመጋዘኑ ኃላፊዎች አብዛኛውን ግዜ በፊርማ የሚረጋገጥ አለመሆኑና በተጨማሪም በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ በሲሚንቶ ማከማቻ መጋዘን ቁጥጥር ባለመኖሩ በአካል መቁጠር የተቻሉ 22 የሙገር ሲሚንቶ ከረጢቶች ፈንድተው የታዩ ሲሆን መቁጠር የማይቻልም በመጋዘኑ ወለል ማየት መቻሉ፣

79. በከሰም ግድብና መስኖ ልማትና በሞጆ ደረቅ ወደብ ፕሮጀክቶች ድርጅቶቹ ሥራ ከጀመሩባቸው ዓመታት ጀምሮ ካሊብሬት ተደርገው የማያውቁ መሆኑ፣.

80. የመሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች ግዥ ከመፈፀሙ በፊት የመለዋወጫ አቅርቦት መኖርን ከማረጋገጥ አኳያ፡- በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት ከብረታብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን የተገዙ የሻንቱ/SHANTU/ ዶዘሮች መለዋወጫ ችግር እስካሁን ያልተፈታ ሲሆን የፋኦ/FAw/ ገልባጭ መኪኖች አብዛኛውን ግዜ በብልሽት ምክንያት ሥራ የማይሰሩ መሆኑ ከሥራ ስምሪት መቆጣጠሪያ ማስረጃ መረጃ የተገኘ መሆኑ፣

81. ድርጅቱ አገልግሎት ላይ የማይውሉ መሳሪያዎችን፣ ተሽከርካሪዎችንና መለዋወጫዎችን በድርጅቱ አወጋገድ መመሪያ መሰረት ብዛታቸው 81 የሆኑ በብር 3487692.98 በታህሳስና በጥር 2007 ዓ.ም የሸጠ መሆኑና በ 2008 ዓ.ም ብዛታቸው 173 የሆነ አገልግሎት ላይ የማይውሉ ለመሸጥ ማቀዱ በበጎ ጅምር የሚታይ ሲሆን ከብዛታቸው አንፃር አፋጣኝ እርምጃዎች መውሰድ የሚያስፈልገው መሆኑ፣

82. በድርጅቱ የሚካሄድ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ/Inventory/ ውሳኔ አሰጣጥን በተመለከተ በከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት በ 2006 ዓ.ም በተደረገ የፕሮጀክቱ ንብረት ቆጠራ መብለጥና ማነስ የታየባቸው በሚመለከተው ኃላፊ ውሳኔ ያልተሰጣቸው መሆኑ፣

83. በድርጅቱ የግዥና ንብረት አስተዳደር መረጃዎች ልውውጥን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አሰራር ከመጠቀም አንፃር የድርጅቱ ዌብ ሳይት መለቀቁ ቢገለፅም የዳታ ቤዝ የማዘጋጀት ሥራ በጅምር ያለ መሆኑ፤ እንዲሁም በከሰም ግድብና መስኖ ልማትና በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክቶች ያልተተገበረ መሆኑ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ክፍል አራት

በክትትል ኦዲቱ (Follow up Audit) የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች

በ 2005/2006 ዓ.ም በኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት በግዥና ንብረት አስተዳደር አፈፃፀም ላይ ለድርጅቱ በቀረበ ሪፖርት የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች አብዛኛው ተግባራዊ የተደረጉ ቢሆንም የተወሰኑት ተግባራዊ ያልተደረጉ በመሆናቸው ድርጅቱ ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲተገበሩ እንዲያደርግ በድጋሚ የሚከተሉት የማሻሻያ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

84. ድርጅቱ አጣዳፊ በሚል ምክንያት ከድርጅቱ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች የሚቀርቡለትን የግዥ ጥያቄዎች በዋጋ ማቅረቢያ ስልት/Proforma/ ከማስተናገድና አልፎ አልፎም ድርጅቱ ካስቀመጠው የዋጋ ማቅረቢያ ጣሪያ ብር 132,000 ግዥ ከመፈፀም ጠያቂ ክፍሎችን በዓመታዊ እቅድ እንዲካተቱ በማድረግ የጥቅል ግዥ ተጠቃሚ ሊሆን ይገባል፡፡
85. በድርጅቱ የመለዋወጫ ግዥ በአብዛኛው ከብቸኛ አቅራቢዎች በቀረበ ፕሮፎርማ ኢንቮይስ በመሆኑ ድርጅቱ ሌሎች አማራጮችን ለማየት በውድድር ሊያሳትፍ ይገባል፡፡
86. ድርጅቱ በሞጆ ደረቅ ወደብ ግንባታ ፕሮጀክት የግዥ አፈፃፀም ሁኔታ ላይ ቼክ በአሸናፊ ድርጅት ስም የሚዘጋጅበት ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡
87. ድርጅቱ በፕሮጀክት በሚገኙ መጋዘኖቹ በግዥ፣በእርዳታ ወይም በስጦታ መልክ ያገኛቸው ቋሚና አላቂዎች በእስፔስፊኬሽን መሰረት ስለመሆናቸው በኢንስፔክሽን ስርዓት እንዲረጋገጡ ማድረግ አለበት፡፡
88. ድርጅቱ በሚጠቀምበት እስቶክ ካርድ ላይ የዝቅተኛና የከፍተኛ ክምችት/Minimum & Maximum level/ መጠን ሊቀመጥ ይገባል፡፡
89. ንብረቶች ከመጋዘን ወጪና ገቢ ሲደረጉ በሚመለከታቸው የመጋዘኑ ኃላፊዎች በተሟላ ሁኔታ በፊርማ መረጋገጥ አለባቸው፡፡
90. የሲሚንቶ መጋዘኖች ሰራተኞች ሲሚንቶን ወደ መጋዘን ሲያስገቡም ሆነ ለሥራ ወጪ ሲያደርጉ በሥራው ሂደት ምን ያህል የሲሚንቶ ከረጢት እንደፈነዳ የመጋዘን ኃላፊዎች በመመዝገብ ለበላይ ኃላፊዎች ሪፖርት የሚያደርጉበት ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡
91. ድርጅቱ በፕሮጀክት የሚገኙ የነዳጅ ታንከሮችን በሚመለከተው የመንግስት አካል ካሊብሬት ሊያስደርግ ይገባል፡፡

92. ድርጅቱ ለሥራ የሚያስፈልጉትን የግንባታ መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎችን ከመግዛቱ በፊት የመለዋወጫ አቅርቦት መኖሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡

93. ድርጅቱ አገልግሎት ላይ የማይውሉ መሳሪያዎችን፣ተሽከርካሪዎችንና መለዋወጫዎችን ከማስወገድ አንፃር የሰራቸው ሥራዎች አበረታች ቢሆኑም ካላቸው ብዛት እንፃር በአፋጠኝ ሊያስወግዳቸው ይገባል፡፡

94. በድርጅቱ ስር በሚገኙ ፕሮጀክቶች ለሚደረግ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ መብለጥ ወይም ማነስ ለሚታይባቸው በድርጅቱ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ውሳኔ ሊሰጡ ይገባል፡፡

95. ድርጅቱ የግዥ እና ንብረት አስተዳደርን መረጃ ልውውጥ ዘመናዊ ከማድረግ አኳያ ቴክኖሎጂ መጠቀም አለበት፡፡

አባሪ 1

በ2005-06 ዓ.ም በክዋኔ ኦዲቱ ቀርበው የነበሩ የማሻሻያ ሃሳቦች

- ድርጅቱ ለሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት በቅድሚያ የግዥ እቅድ በማዘጋጀት የዋጋ ቅናሽና የጥራት ተጠቃሚ የሚያደርገውን የግዥ ስልት በመለየት ግዢ መፈጸም ይኖርበታል፡፡
- ድርጅቱ በግዢ ዕቅዱ መሰረት በጥቅል ወይም በቅንጅት ሊገዙ የሚገባቸው ግዥዎችን በመለየት በጥቅል መግዛት ይገባዋል፡፡
- ድርጅቱ በቼክ ክፍያ ሲፈጽም ቼክ ባሸነፈው አቅራቢ ድርጅት ስም ሊዘጋጅ ይገባል፡፡
- ድርጅቱ በፕሮፎርማ ግዥ ሲፈጽም በአቅራቢዎች ዘንድ የተወዳዳሪነት መንፈስ እንዲኖር እና በዝቅተኛ ዋጋ ጥራት ያለው አቅርቦት ለማግኘት እንዲቻል ብቸኛ አስመጪዎችን እና ሌሎች ህጋዊ ፈቃድ እና እውቅና ያላቸውን ድርጅቶች በመለየት በግዢ መመሪያው መሰረት ቢያንስ ከሶስት ድርጅቶች ፕሮፎርማ ሰብሰቦ በማወዳደር ግዢ ሊፈጽም ይገባል፡፡
- የግዥ ፕሮፎርማ መሰብሰብ እና ግዥውን የመፈጸም ሥራ፣ ንብረቶች ተገዝተው ሲመጡ ገቢ የማድረግ እና የገቢ ሰነዶችን የማዘጋጀት እና ንብረቶቹን ወጪ የማድረግ እና የወጪ ሰነድ የማዘጋጀት ሥራ በተለያዩ ሰራተኞች እንዲከናወኑ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ድርጅቱ ለኪራይ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች የሚያወጣው ወጪ አዋጭ መሆኑ በቅድሚያ የአዋጭነት ጥናት /Cost Benefit Analysis/ ተሰርቶ ሊረጋገጥና በሚመለከተው የሥራ ክፍል ሊወሰን ይገባል፡፡ ከኪራይ መሣሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች ተገቢው አገልግሎት ስለመገኘቱ በቅርብ ኃላፊው ክትትል በማድረግ በየወሩ ትክክለኛ የሆነ ሪፖርት ለዋና መ/ቤት ሊደርስ የሚችልበትን ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ድርጅቱ በግዥ፣ በእርዳታ እና በስጦታ ያገኛቸውን ቋሚና አላቂ እቃዎች በእስፔፊኬሽናቸው መሰረት መሆናቸውን ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት /ባለሙያዎች/ እየተረጋገጠ ገቢ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በድርጅቱ የሚገኙ ዕቃዎች በአቀማመጥ እና አያያዝ እንዳይበላሹና በሰው ልጅ ጤንነት እና በአካባቢ ላይ ችግር እንዳያስከትሉ እንደ እንቅስቃሴያቸው ፍጥነት፣ አዲስ፣

የሚያገለገሉ፣ የማያገለግሉ፣ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ፣ እንዲሁም እንደተፈጥሮ ባህሪያቸው እንዲያዙ እና እንዲቀመጡ መደረግ አለበት፡፡ በክምችት የሚያዙ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያላቸው ንብረቶች ተለይተው ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠን /Minimum & Maximum Stock Level/ ሊቀመጥላቸው ይገባል፡፡

- ❖ የድርጅቱ ንብረቶች ገቢና ወጪ ሲደረጉ የገቢና የወጪ ሰነዶች ሊሟላላቸው እና በሚመለከተው ኃላፊ እንዲጸድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ❖ የድርጅቱ መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች የሚፈለገውን አገልግሎት እንዲሰጡ ግዥ ከመፈጸሙ በፊት አሰፈላጊው የጥገና እና የመለዋወጫ አቅርቦት መኖሩ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
- ❖ ለድርጅቱ ተበላሽተው ያለሥራ ጋራዥ የቆሙት 469 ዶዘሮች፣ ኤክስካቫተሮች፣ ግሬደሮች፣ ሎደሮች፣ ገልባጭ መኪናዎች፣ ኮምፓክተሮች፣ ደብል ካፕ መኪናዎች እና የተለያዩ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች የብልሽታቸው መንስኤ እየተጣራ ተጠግነው ሥራ ላይ ሊውሉ ወይም ሥራ ላይ ሊውሉ የማይችሉ ከሆነ በባለሙያ ተጠንቶ በድርጅቱ የአወጋገድ መመሪያ መሰረት ሊወገዱ ይገባል፡፡
- ❖ ድርጅቱ የተሽከርካሪ፣ የማሽነሪ እና የግንባታ መሳሪያዎች የነዳጅ አጠቃቀምና የስምሪት መመሪያ ሊያዘጋጅና እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ❖ በድርጅቱ አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎች፣ መለዋወጫዎች እና የግንባታ ቁሳቁሶች በባለሙያ ተጠንቶ በድርጅቱ የአወጋገድ መመሪያ መሰረት ሊወገዱ ይገባል፡፡
- ❖ ድርጅቱ በየአመቱ በሚያደረገው የንብረት ቆጠራ በማነስም ሆነ በመብለጥ ለሚታዩ ልዩነቶች ለሚመለከተው ኃላፊ እየቀረበ ወቅታዊ የእርምት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡
- ❖ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር መረጃዎች ለቁጥጥር እና ክትትል እንዲያመች፣ መረጃዎች በቀላሉ ለመለዋወጥ እንዲያስችል፣ ለድርጅቱም ሆነ ለሶስተኛ ወገን በወቅቱ በተቀላጠፈ ሁኔታ የመረጃ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል በዘመናዊ ተክኖሎጂ ሊደገፉ ይገባል፡፡